የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ፃ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፯ አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No 47
ADDIS ABABA, 22th May, 2025

**<u>ማውጫ</u>**

**<u>Content</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፯/፪ሺ፲፯

ለአካባቢያዊና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ………....ገጽ ፲፰ሺ፬፻፶፯

proclamation No. 1377/2025

Italian Republic Loan Agreement for Budget Support Programme for Environmental and Green Economy Development Ratification Proclamation…………………….. page 18457

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፯/፪ሺ፲፯

## <u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

ለአካባቢያዊና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፩ ሚሊዮን ፭፻ሺህ ዩሮ (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ነሐሴ ፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 1377/2025

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ITALIAN REPUBLIC</u>

**WHEREAS**, the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Eleven Million Five Hundred Thousand Euro (11,500,000 Euro) for Budget Support Program for Environmental and Green Economy Development was signed on the 12th day of August 2024;

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ፳፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአካባቢያዊና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፯/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ነሐሴ ፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር F.ROT/AID 24/003/00 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፩ ሚሊዮን ፭፻ሺህ ዩሮ (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said loan agreement at its 29th regular session held on 13th day of May 2025;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Italian Republic Loan Agreement for Budget Support Programme for Environmental and Green Economy Development Ratification Proclamation No. 1377/2025".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number F.ROT/AID 24/003/00 signed on the 12th day of August 2024 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an equivalent to Eleven Million Five Hundred Thousand Euro (11,500,000 Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

፬.**<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፯**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 22th Day of May, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**